# በእነ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ንግግር አንድምታ ላይ የኦነግ እጅግ የሳሳተ ዕይታ!

እነ ፕሮፌሰር (ሊቀ ማእምራን) ብርሃኑ ነጋ ትናንትና በዋሽንግተን ዲሲ የነበረውን መግለጫ ማብራሪያና ከዚያም የጥያቄና መልስ ውይይት በመመርኮዝ ኦነጎች ወዲያውኑ ተሽቀዳድመው አንድ የቀድሞው የኦነግ አመራር አባል ቡሩ በራቃ ነኝ ባሉ ግለሰብ በኩል "የብሔር ማንነት ጭቆና አበቃም አላበቃም የማይለወጥ ማንነት ነው ምላሽ ለኣርበኞች ግንቦት 7 ቱ ሊቀመንበር ለዶክተር ብርሃኑ ነጋ'' በሚል ርእስ አቋም አስተሳሰባቸውን መግለጻቸው ይታወሳል ፡፡

ነገሩ እንዲያው ግርም ቢለኝና ገለጥለጥ ማለት ያለባቸው ነገሮች ስላሉ እኔም የሰዎቹን ሐሳብ በመፈተሽ ጥቂት ልልበት በመፈለግ ጉዳዩን አነሣሁት፡፡

ሰውየው ወይም ሰዎቹ (እነ ኦነግ) የብሔር ፖለቲካን በተመለከተ ዶክተር ብርሃኑንና ድርጅታቸውን በቀድሞው ስምና ኃላፊነት እየጠቀሱ ማለትም "አርበኞች ግንቦት ሰባት" በማለት ሳይሆን "ግንቦት 7'' በማለት ብቻ ድርጅቱን የተለየ አቋም ያንጸባርቃሉ ብለው ጠብቀው እንደነበር ነገር ግን ከዶ/ር ብርሃኑ ንግግር እንደተረዱት ድርጅቱ በቀድሞው ሐሳቡ በመጽናት "ድርጅቱ ዛሬም የብሔር ማንነትን እንደ አፍራሽ ፖለቲካ መመልከቱን እንደቀጠለ በሊቀመንበሩ ንግግር በሚገባ ተንጸባርቋል'' ይሉና ቀጠል አድርገውም "በዚህ ላይ ዶክተር ብርሃኑ ሲናገሩ 'የዘውግ ማንነት' ፖለቲካን የወለደው የዴሞክራሲ እጦት ስለሆነ ዴሞክራሲ ከሰፈነ 'የዘውግ ፖለቲካ' ተወግዶ ወደ ዜግነት እኩልነት ፖለቲካ መሸጋገር እንደሚቻል ያላቸውን እምነት ገልጠዋል" በማለት የጠበቁት ሳይሆን በመቅረቱ ማዘናቸውን በመግለጥ ለመተቸት ሞክረዋል፡፡

እኔ በእውነት እነኝህን ሰዎች በአካል አግኝቶ መጠየቅ ብችልና ሊመልሱት የሚችሉት ነገር ካለም ከአንደበታቸው እሱን መስማት ብችል ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር፡፡ ይሁንና እስኪ ባሉበት እንደሚደርሳቸው ተስፋ ላድግርግና እነኝህ ሰዎች ለራሳቸው ለሰውነታቸው ክብር ያላቸው ከሆኑ፣ ለአመክንዮ (ለሎጅክ) ለሞራል (ለቅስም) ለፍትሕ ድንጋጌዎች እራሳቸውን የሚያስገዙ የሠለጠኑ ሰዎች ከሆኑና የእውነት ልዕልናን የሚቀበሉ ከሆኑ ይመልሷቸው ዘንድ የምሻቸው ጥያቄዎች አሉኝና እነሱን ላቅርብ፡-

ሲጀመር "የብሔር ማንነት ፖለቲካ" ማለት ምን ማለት ነው? ይሄን በተመለከተ እናንተን የገባቹህና እኛንም እንዲገባን የምትፈልጉት ምንድን ነው? ይሄንን እንድትመልሱልኝ የምፈልገው ዘልማዳዊ በሆነው መንገድ ሳይሆን ሳይንሳዊ (መጣቃዊ) በሆነ መንገድ ነው፡፡ "የሞኝ ዘፈን ሁልጊዜ አበባየሁ" ዓይነት እንዲሆን አይፈለግም፡፡ መቸስ በሀገርና በሕዝብ እጣ ፋንታ ላይ በሚወስን ጉዳይ ላይ ነውና እየተወያየን ያለነው ውይይት ንግግራችን በዚህ ደረጃ እንዲሆን መፍቀድ እንዳለባቹህ ነጋሪ ሊያስፈልጋቹህ የሚገባ አይመስለኝም፡፡ ውይይቱ ሳይንሳዊ (መጣቃዊ) የሆነ ይዘት ይኖረው ዘንድ ግዴታ ነው ማለቴ ነው፡፡

"የብሔር ማንነት ፖለቲካ" ስትሉ እናንተ "የኦሮሞ" ትላላቹህና እውን እንደምትሉት በትክክል ብሔረሰብ የሚባለው ነገር በተጨባጭ ሕልው የሆነ ነገር ስለሆነ ነው የብሔር ፖለቲካን እያቀነቀናቹህ ያላቹህት? እርግጠኛ ሆኘ የምነግራቹህ አለ ብላቹህ ስለምታምኑ አይደለም ይሄንን እያደረጋቹህ ያላቹህት፡፡ በዚህ ዘመን የብሔረሰብ ሕላዌ ውሸት እንደሆነ ታውቃላቹህ ግን ግላዊና ቡድናዊ የጥፋት ዓላማቹህ ከዚህ ዘውጋዊ አስተሳሰብ ውጪ መውደቂያ ስለሌለው ነው ዘውገኛ አስተሳሰብን ሙጥኝ ያላቹህት፡፡

እናንተ ለኦሮሞነታቹህ ማረጋገጫው ምንድን ነው? መቸስ ማንም ሰው ነተሥቶ እኔ ኦሮሞ ነኝ ቢል ሊሆን እንደማይችል የምታውቁ ይመስለኛል፡፡ ያ ቢሆን ባልቸገረ ነበር፡፡ ከሆነ ዘንዳ የኦሮሞነት መስፈርቱ መለኪያው ምንድን ነው? ኦሮሞ የተለየ ደም ያለው ከሰው ልጆች ወገን ያልሆነ ከሌላ ዓለም (ፕላኔት) የመጣ ፍጡር ነው ወይ?

ከእናንተ መሀል የሌላ ብሔረሰብ ወይም ጎሳ ደም የለብኝም ብሎ አፉን ሞልቶ መናገር የሚችል ሰው አለ ወይ? የማናውቅ ይመስላቹሀል እንዴ! ብዙዎቻቹህ በእናት ወይም በአባት ከሌላ ብሔረሰብ ወይም ጎሳ የተወለዳቹህ አይደላቹህም እንዴ! መሰላቹህ እንጅ ብዙዎቻቹህ እንዲያውም በሲሦም እንኳን ኦሮሞነት የሌለባቹህ አይደላቹህም እንዴ! ምን እንደምታወሩ ግን በቅጡ ትገነዘቡታላቹህ? ጆሯቹህ አይሰማም ድፍን ነው እንዴ? ጭንቅላታቹህ አያስብም አያንሰላስልም ድንጋይ ነገር ነው እንዴ? የእናንተኑ ጩኸት ብቻ ነው መልሶ ለእናንተው የሚያስተጋባው?

ካልሆነ ታዲያ ለእንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ መልስ መስጠት ትችላላቹህ? መልሳቹህ ምንድን ነው? ፈጽሞ ለዚህ ትክክለኛውን መልስ መስጠት አትችሉም፡፡ እንዴት ከእናንተ ማንነት እንኳን ተነሥታቹህ ብሔረሰብ የሚባለው ነገር በስም ካልሆነ በስተቀር በአካል የሌለና ተጨባጭ ያልሆነ እንደሆነ አረጋግጣቹህ፤ የዚህን ያህል መልስ ለመስጠት እንኳን የማያስችልን አስተሳሰብ የፖለቲካቹህ መሠረት አድርጋቹህ የሀገርና የሕዝብ እጣ ፋንታ በዚያ እንዲወሰን ማድረግ ስሕተት እንደሆነ እንዴት መረዳት ይሳናቹሀል? ቀይና ቢጫ ሲቀላቀሉ ብርቱካንማ ይሆናሉ እንጅ ከተቀላቀሉ በኋላ ቀይ ወይም ቢጫ አይደሉም፡፡ የቀይና የቢጫነታቸው ህልውና ከተቀላቀሉ በኋላ አክትሞለታል፡፡ ብርቱካንማ ቀለም እኔ ቀይ ብቻ ነኝ ወይም ቢጫ ብቻ ነኝ ካለ መልሱ ትክክለኛና መጣቃዊ (ሳይንሳዊ) አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን የሰውየው የጤንነት ጉዳይም አጠያያቂ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡

ይሄንን ቀላል ስሌት እኮ ነው መረዳት የተሳናቹህ፡፡ እናንተ እኮ እንዲህ የዞረባቹህ ከእውነታ ጋር የተጣላቹህ የተራራቃቹህ እውነታን መቀበል ለእውነታ መገዛት የማትፈልጉ ይሄ አቅልና ችሎታ አቅም ብስለት ጨርሶ የሌላቹህ እኮናቹህ! እኛ ታዲያ ችግራችን ምን ሆነና? ይሄ አስተሳሰብ ትክክለኛና ሳይንሳዊ አለመሆኑ አይደለም ወይ እንዳንቀበለው እንድንንቀው ያደረገን፡፡ ሳይንሳዊና ልዕልና ያለው ሐሳብ ሆኖ እያለ ልንቀበል የማንችልበት ምክንያት ምን አለ ታዲያ? እጅግ የማዝነው እየነገርኳቹህና መልስ አጥታቹህም እንኳን አሁንም የማትማሩ የማትለወጡ መሆናቹህን ሳስብ ነው፡፡ ድንጋይ ቢቀቅሉት ይበስላል? እንደዛ ናቹህ፡፡

አይ! አይደለንም እኛ ማሰብ ማገናዘብ እንችላለን የምትሉ ከሆነ ደግሞ ይሄንን የጥፋት አስተሳሰብ ወርውራቹህ በመጣል አሳይታቹህ አረጋግጡ! እራሳቹህን አብስሉ! ከዘመኑ ጋር የሚሔድ አስተሳሰብን ጨብጡ፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰው ያለ እንደሆነ፤ ኦሮሞ ከአንዱ የሰው ልጅ ምንጭ በተለየ ሁሌታ ሌላ የራሱ ምንጭ ያለው እንደሆነና ይሄንን ማረጋገጥ ከቻላቹህ ብቻ ነው አባባላቹህ ትክክል ሊሆን የሚችለውና እኛም ይሄንን የመቀበል ግዴታ የሚኖርብን፡፡ ስለብሔረሰብ ማንነትና ጥቅም መሟገት መታገላቹህም ትክክል የሚሆነው፡፡

እናሳ ኦሮሞ ከሌላ ዓለም ነው ተፈጥሮ የመጣው፣ ደሙም ከሰው ልጆች ደም ጋር ግንኙነት የለውም የሚለውን ልታረጋግጡልን ትችላላቹህ? ያልበሰላቹህ የምንለው ለዚህ ነው፡፡ “የያዝነው አቋም ትክክል ነው እንሞትለታለን!” ለማለት አስቀድማቹህ እነኝህን ነጥቦችን በአግባቡ መመርመርና መመለስ ይጠበቅባቹሀል፡፡

ከዚህ ውጭ ግን እናንተ ከዘመኑ ጋር የማይሔድ ዘገምተኛ አስተሳሰብ የያዛቹህ እንደሆነ ጭራሽ እኛን “ለምን አልተቀበሉንም! ለምን እኛን አልመሰሉም!” እያላቹህ አታድክሙን፡፡ ደሞ እኮ ምሳሌ ተገኝቶ ተሙቶ አሜሪካንና አውሮፓም ውስጥ ስንት ብሔር ተኮር ፖለቲካ አጥፊ ስለሆነ ከፖለቲካ ጨዋታቸው ውጭ ያደረጉ፣ አስተሳሰቡ የተሳሳተና ኋላ ቀር መሆኑን የሚያሳዩ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ የተሻሉ ስንት ሀገራት እያሉ አስተሳሰባችንን ይደግፍልናል ብለው በማሰብ ፈልገው ፈልገው ምን አሉ፡-

““ እንደ አርበኞች ግንቦት ሰባቱ ሊቀመንበር ቁንፅል አቋም ከሆነ ወያኔ በጋራ ትግል ከተወገደ በኋላ ኦሮሞው ኦሮሞ ነኝ ብሎ

ራሱን መጥራት አቁሞ ‘ኢትዮጵያዊ ነኝ’ በሚለው አመለካከት ብቻ እንዲጸና ይፈለጋል። ይህ ደግሞ ከቶ ሊሆን አይችልም።

የሊበራል ዴሞክራሲ ሐዋሪያ የሆኑት እነ እንግሊዝ እንኳዋን የብሔር ማንነትን በቱባው ዴሞክራሲያቸው ስኬት ማስቀረት አልቻሉም። እንደዛ ቢሆንማ ዛሬ ዩናይትድ ኪንግደም መባል ባላስፈለጋቸው ነበር። ኢንግሊሽ፣ ዌልሽ፣ ስኮትሽና አይርሽ እያሉ በብሔራቸው ማንነት፣ በቋንቋቸውና በጂኦግራፊያዊ አሰፋፈር መሸንሸን ባላስፈለጋቸው ነበር። የዴሞክራሲያቸው መዳበር ይበልጥ የብሔር ምንነታቸውን አስከበረው እንጂ አልናደውም። ከአንድ ዓመት ገደማ በፊት በስኮትላንድ የተካሔደውን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ውሳኔ ሕዝብን ማስታወስ ብቻ ለዚህ ሐቅ በቂ ምስክር ነው። ለኢትዮጵያ

አንድነት ከማንም በላይ እንቆረቆራለን የሚሉት የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ከዓለማችን ፖለቲካ ልምድ መቅሰም አይፈልጉም። በሚመኙትና በለመዱት የጭለማው ዘመን ሁኋላ ቀርና ነውረኛ የፖለቲካ አመለካከት ብቻ ሕዝቦችን ሸብበው መቀጠል ያልማሉ። ይህ ደግሞ ከምንም ከማንም በላይ እንቆረቆርላታለን ለሚሏት የኢትዮጵያ አንድነት አደገኛ ነው"" ብለው አረፉት፡፡

አየ እናንተ! ሲጀመር እንግሊዝ ማለትና ዩናይትድ ኪንግደም ማለት አንድ አይደሉም እሽ? መጀመሪያ ልዩነታቸውን አጣርታቹህ እወቁ፡፡ ሲቀጥል ለመሆኑ እነ ዌልሽ፣ ስኮትሽና አይርሽ ከያሉበት ምድራቸው ጋር ያላቸውን የማንነት ትስስርና ታሪካዊ ዳራ እናንተ ኦሮሚያ ከምትሉት የሀገራችን ክፍልና ኦሮሞ ከምትሉት ብሔረሰብ የማንነት ትስስር ታሪካዊ ዳራ ጋር ምን የሚያገናኛቸው ምን የሚያመሳስላቸው ነገር ኖሮ ነው ትንሽም እንኳን ሳታፍሩ ይሄንን ምሳሌ ብላቹህ የምትጠቅሱት? የፈጠራ ወሬያቹህን ደጋግማቹህ ስታወሩት ጊዜ ጭራሽ ለእናንተም እውነት መስሎ ታያቹህና እንዴ ልብ ወለድ ድርሰታቹህን ጭራሽ ሌላውም እውነት አድርጎ ቆጥሮ በዚህ መሠረት እንዲከወን የምትፈልጉት? ኧረ እንዲያው በጣም ይገርማል መንጋ ንክ ሁላ!

ከእነ ዌልሽ፣ ስኮትሽና አይርሽ ጋር እራሳቹህን አመሳስላቹህ እነሱ ዩናይትድ ኪንግደም (የተባበሩት የንጉሥ ግዛቶች) በመባል ከእንግሊሽ ጋር ካላቸው ግንኙነት ጋር ለማመሳሰል አስቀድማቹህ የእናንተ ማንነት በዚህች ሀገር የሚጀምረው ይህች ሀገር እንደ ሀገር ከመመሥረቷ በፊት ነው ወይስ በኋላ? በደቡብና በምሥራቅ በኩል ካለው ድንበር ወዲህ አሁን ኢትዮጵያ ተብላ ተከልላ ካለችው ሀገር ጋር ትስስራቹህ የሚጀምረው መቸና እንዴትስ ነው? ይሄ ነው ቁልፉ ጥያቄ እሽ? ይሄ ነው እናንተን ከእነ ዌልሽ፣ ስኮትሽና አይርሽ ጋር ሊያመሳስላቹህ እንዳትችሉ የሚያደርጋቹህ እሽ? የዚህ ጥያቄ መልስ እናንተን ተጠቃሚ ስለማያደርጋቹህ ነው ጠላቶቻችን የፖለቲካ (የእምነተ አሥተዳደር) አስተሳሰባቹህን ሲቀርጹላቹህ "ኢትዮጵያ የተፈጠረችው ከመቶ ዓመታት ወዲህ ነው" በማለት ይሄንኑ አስጠንተው እንድታላዝኑት ያደረጓቹህ፡፡ ይሁን እንጅ ታዲያ ከእውነታ ጋር የተጣላቹህ ለሀቅ ፊታቹህን ያዞራቹህ እናንተ የንኮች መንጋ ሆይ! ይሄንን ክህደትና ፈጠራ እንንተ ስላላዘናቹህ የሚሆን ይመስላቹሀል እንዴ? የኢትዮጵያ ሕዝብ ጆሮ የሚሰመማቹህ ይመስላቹሀል እንዴ?

ይሄንን ጉዳይ ከእውነታ ጋር አገናዝባቹህ እንደሰው አስቡና እንደሰውም ለመመለስ ሞክሩና እስኪ "ይሄንን የማድረግ መብት አለን ወይ?" ብላቹህ እራሳቹህን ጠይቁ? ለምሳሌ እዛ ተሰዳቹህ ያላቹህበትን ሀገር የመገንጠል መብት እንዳላቹህ ታስባላቹህ ወይ? መቸም አዎ! እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በሚገርማቹህ ሁኔታ አሁን እያላቹህ ያላቹህት ግን ይሄንን ነው፡፡ ሲጀመር አማራው ትግሬው ሌላውም እርስ በእርሱ ተቀላቅሎ ተዋልዶ ተዋሕዶ አንድ ኢትዮጵያዊ ማንነት እንደፈጠረ ሁሉ ኦሮሞም ከእነዚህ ጋር ተዋሕዶ ተዋልዶ ተቀላቅሎ ኢትዮጵያዊ ማንነትን ተላብሷልና በዚህች ሀገር በአሁኑ ጊዜ የትኛውም ብሔረሰብ ስሙ ብቻ እንጅ አካላዊ ህልውና የለውም!
ከዚህ ሁሉ ድንቁርናቹህ ጀርባ የጠላቶቻችን እጅ በተለይም የሸአቢያ እጅ ስላለ እራሳቹህን በቀላሉ ከእነሱ ቁጥጥር ነጻ ልታደርጉ እንደማትችሉ፣ እንደፈለጉ እንዲያደርጓቹህ ፈቀዳቹህላቸዋልና ነው የቱንም ያህል እውነት ቢነገራቹህ ልትለወጡ እንደማትችሉ ከላይ የተናገርኩት፡፡ ከሸአቢያ ጋር ያላቹህ ግንኙነት የዛሬ ወይም የትናንት አይደለም፡፡ የከትናንት መስቲያ እንጅ፡፡ ያለእሱ ትዕዛዝና ምክር የፈጸማቹህትና የምትፈጽሙት አንዳችም ነገር ኖሯቹህ አያውቅም፡፡
ከወራት በፊት "ግልጽ ማሳሰቢያ ለሕዝባዊ ግንባርና ለመሪው አቶ ኢሳይያስ አፈወርቂ!" በሚል ርእስ አንድ አጭር ጽሑፍ መጻፌ ይታወሳል፡፡ ሸአቢያ ለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ የሰጠውን ምላሽ ዓይታቹህል፡፡ እርግጠኛ ነኝ ይሄንን ጥያቄ አርበኞች ግንቦት ሰባትም ለሸአቢያ አንሥቶታል፡፡ አሁንም እርግጠኛ ነኝ መልስ አልሰጣቸውም ወደፊትም አይሰጣቸውም፡፡

አዳዲስ ተገንጣይ ድርጅቶችን መሥርቶ ከኦነግና ከኦብነግ ጋር ኖርዌይ ኦስሎ ላይ ኢትዮጵያን ተባብረው የማፍረስ ዓላማን አንግበው ጥምረት እንዲመሠርቱ ያደረገው ሸአቢያ ነው፡፡ መቀመጫቸው አስመራ ሆኖ እያለ ኦስሎ ሔደው ጥምረቱን መመሥረታቸውን እዚያ እንዲያውጁ ያደረገው ከዚህ ጀርባ ያለው እሱ መሆኑ እንዳይታወቅ ነው፡፡

ብዙዎቻቹህ እንደሚመስላቹህ ያ ነፈዝ ተስፋዬ ገብረአብ በማንነት ቀውስ ውስጥ እየተሰቃየ ያለ የሥነልቡና ሕመምተኛ ስለሆነ አይደለም ባለፈው “ትግሬነቴን ትቸ ከዚህ በኋላ ኦሮሞ ሆኛለሁ! ስሜም ሞጋሳ ነው” ያለውና እንደምታዩት ከኦነግ ጋር አብሮ እየዶለተ ያለው፡፡ ሸአቢያ አዲስ ተልእኮ ስለሰጠው እንጅ፡፡ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ እያለም እነዚያን ብሔረሰብን ከብሐየረሰብ ጋር ለማባላት ያሴሩ መርዘኛ ልብወለድ ድርሰቶችን የጻፈውና ወያኔ እንዲያሳትመው ያደረገው በሸአቢያ ትእዛዝ ነበር፡፡

ይሄ ሁሉ እንዳለ ባውቅም በሸአቢያ ላይ እንጥፋጣፊ ተስፋ እንኳን እንደሌለ ባረጋግጥም አሁንም በአርበኞች ግንቦት ሰባት ትግል ተስፋ አልቆርጥም፡፡ ቀድሞም ቢሆን “አማራጭ የለምና ከመርዘኛ እባብ ጋር እንዳላቹህ እያሰባቹህ ከእባብ ጋር ያለ ሰውን ጥቃትና ጥንቃቄ ይዛቹህ ተሠማሩ” አልኩ እንጅ ሸአቢያን እንመነው ልባችንን እንስጠው ብየ እንደማላውቅ ይታወቃል፡፡ መርዘኛ እባብ የቱንም ያህል አደገኛ ቢሆንም አቀራረቡ ከታወቀበት እየደነሰ እንዲያዝናና ማድረግም ይቻላልና፡፡ እዚህ የማልናገረው በባለ ታሪከ ብዙው እግዚአብሔር እጅ ያለ ሌላ ብዙ ነገር አለና፡፡

እነ ፕሮፌሰር (ሊቀ ማእምራን) ብርሃኑ ይሄንን ያህል ከባድ ጥንቃቄ፣ ንቃት፣ ብስለት፣ ትጋት፣ ጥረት፣ መሥዋዕትነት ለሚጠይቅ እጅግ አድካሚና አደገኛ ተልእኮ ውስጥ ነውና ያሉት እባካቹህ እነሱን የምትኮንኑ የምታወግዙ ያልገባቹህ ወገኖች ሆይ! እባካቹህ ስለ ፈጠራቹህ አምላክ ብላቹህ! አፋቹህን ያዙላቸው፣ ተረዷቸው፣ ከቻላቹህ ንቁና አይዟቹህ በርቱ በሏቸው ደግፏቸው ካልቻላቹህ አታደናቅፏቸው? እንደመሰላቸው ያድርጉት ከእነሱ በላይ ጉዳዩን ልትረዱት አትችሉምና፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com